ጥቅምት 1999 ዓም

የጉባዔ አበው መልዕክት፥ በኮ/አሰውናቀ እንግዳ የድሮ ጠርሠራዊት ባልደረባ

ይድረስ ለኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ሁሉ።

በጦር ትምህርት ቤት እንደ ተማርሁት፥ ወታደር፥ ሀገር እንጅ ጎሳ የለውም

የወታደር ዓላማውና ግዴታው።

1. ዓላማ የውጭ አገር ወራሪ ጠላትን መከላከል

2. ያገር ውስጥ ፀጥታን መጠበቅ በአገር ላይ የሚያምጹ ሽፍቶችንና ጠባብ ጎጠቆችን በቁጥጥር ስር ማድረግ።

3. ግዴታው በአስተዳቀደር አድልዎ የሚያደርጉ ፍትህን የሚረግጡ ሕዝብን በጎሳና በቋንቋ የሚ ለያዩ፥ በሥልጣን የሚባልጉ፥ አሽምሯቸው የጠፋባቸውዕውነትን የተቃወሙና በሥልጣናቸው የሚነግዱትን የመንግሥት መሪዎችን ከሥልጣን አስግዶ ሕዝብ የሚፈልገውን ምንግሥት በዴሞክራሲያዊ መብቱ ተጠቅሞ እንዲያቋቁም ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነትና ግዴታ አለበት።

የሀገራችሁን ሉዓላዊነትና አንድነት ለመጠበቅ የተቋቋማችሁ የሕዝብ አገልጋይ ሠራዊት ሆይ! ታማኝነታችሁ ለሕዝብና ለሀገር መሆን ይገባዋል እንጅ ሕዝብን እየበደሉና ሀገር እየከፋለፈሉ ራሳቸውን ብቻ ለሚያገለግሉ በሥልጣን ላይ ላሉ መሪዎች መሆን የለበትም። የታላቋ ሀገር ሠራዊት እንጅ፥ የቡድኖች አይደለህምና የሕዝብ ሠራዊት መሆንክን ለማስመሰከርክ ግዜው አሁን ነው። በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎችህ በሥልጣን እየባለጉ ሀገር እያጠፉ ሕዝብ ሲበድሉ ዝም ብለህ አትመልከት።እነርሱ ባጠፉ አንተም ከነርሱ ጋር አብረህ እንዳትፈረጅና በታሪክም ተወቃሽ እንዳትሆን አስብበት። ሚናህን ለይ። ህግ ወጥ መሪዎች እነ መለስ ዜናዊ በእናንት በጦር ኃይሎች ደም እየነገዱ ባለፀጋ ሆነዋል። እናንትን በጦት አሳት ውስጠ እየማገዱ በረሃ ለበረሃ እያንከራተቱ፥ እያስራቡና እያስጠሙ፥ እነርሱ የግል ፋብሪካ እያቋቋሙ፥ ታላላቅ ህንፃዎች ይገነባሉ። ልጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ውጭ ሀገር ልከው ያስተምራሉ። የዘረፉትን ገንዘብ በውጭ ሀገር ባንኮች ያስቀምጣሉ።እነርሱ በምቾት እየተንደላቀቁ ሠራዊቱን እየበደሉት ነው።

እነዚህ የጥፋት መልዕክተኞች እነ መለስ ዜናዊ ከሻዕቢያ ቡድን ከነኢስያስ ጋር የነበራቸውን ኢትዮጵያን የመገነጣጠል ሽርክና፥ ኤርትራን ካስገነጠሉና ከነገጣጠሉ በኋላ በሁለቱ ቡድኖች መካከል በነበረው የጥቅም ግጭት ምክንያት በደንበር አሳብበው ሠራዊቱን የእልሃቸው መውጫ በማድረግ ከኤርትራ ወንድሞችህ ጋር አጋድለውህል። ከጦርነቱም ማግስት ብዙዎቹን ከሠራዊቱ እንዲሰናበቱ አድርገው ወርውረው እንደጣሏቸው ታውቃለህ። አንተንም እንደዚሁ ወርውረው ይጥሉሃል።

እነመለስ ዜናዊ፦

- ታላቂቱን ሀገር ኢትዮጵያን ከዘጠኝ ሸንሽነው የጎሳ መንግሥት በማቋቋም የሀገሪቱን አንድነት ከመናዳቸውም በላይ በዜጎች መካከል ያልነበረ የጥላቻ መርዝ መነስነሳቸውን ደጎና አድርገህ ታውቀዋለህ።
- የታላቂቱን ኢትዮጵያ የአምስት ሽህ ዓመት ታሪክ መካዳቸውንም አትዘነጋውም።

- ኢትዮጵያ ተወዳዳሪ ያልነበራትና የረጅም ዘመናት ህልውናዋንክደው የ100 ዓመት ዕድሜ ነው ያላት ማለታቸውነም ታውቀዋለህ።
- የሕዝቡን ቤትና የከተማ ቦታ እየቸበቸቡ የግል መጠቀሚያ ማድረጋቸውንም ታስታውሰዋለህ።
- “ዞሮ ዞሮ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት” እንደሚባለው ትውልድህን ቆጥረህ የምትገባበትን ርስትህን የቀሙህ መሆኑንም ነግ ከነከወዲያ ወርውረው ሲጥሉህ መግቢያ የለህም። ርስት እኮ በባንክ ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ ማለት ነው።

ርስት በሕይወት ሳሉ ይጠቀሙበታል፥ ሲያረጁ ይጦሩበታል፥ ሲሞቱም ለልጆች በመውርስ ይተላለፋል። ርስት ከሌለለ ግን ነፃነትም፥ ክብርም፥ ዜግነትም የለም። የኢትዮጵያ ነፃነት ተጠብቆ፥ የሀገር ሉዓላዊነት ተከብሮ፥ የዜጎች መብት በምንም ሳይረገጥ ለረጅም ዘመናት ለመኖር የቻለው እያንዳንዱ ዜጋ ለርስቱ ዘብ በመቆሙ ነበር። ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ መሿይት እየከፈለ ነፃነቱን ሲያስከብር የኖረው ለርስቱ ሲል እንጅ ለነገስታቱና ለመሳፍንቱ ሥልጣን አልነበረም። ርስት ለሌለው ርስት ከመስጠት ይልቅ፥ እነ መለስ ዜናዊ ባለ ርስትቱን እየነጠቁ የራሳቸው ጢሰኛ አድርገውታል። ( መሬትን መንጠቅ የካፒታሊስት ወይስ የኮሙኒስት ሥርዓት? ቅጡ የጠፋ ነው) ርስት የእምነትና የባህል ምንጭ ነበር። ርስት ሀገር ወዳድ ጀግኖችን የሚያፈልቅና የማንነት መታወቂያ ነበር። ርስት ወኔን የሚገነባ አትንኩኝ ባይነትን ቆራጥነትን፥ መሿይት ደፋርነትን ኩሩነትን ጨዋነትን አልጠቃም ባይነትን ከሁሉም በላይ ለባዕድ በገንዘብ ተገዝቶ አለማጎብደድን በራስ ዕምነት መመካትን ያስገኝ ነበር። ዛሬ በመለስ ዜናዊ ርስት በመነቁና ሁሉም ሀገር የለሽ ጢሰኛ በመሆኑ፥ ለባዕዳን በህልና ዕምነት ተገዥ ሆኗል። ኢትዮጵያዊነትና ባሕል ተዳክሟል። ያስፈራል። ያስደነግጣል።

- በነመለስ ዜናዊ ደካማ አመራር በሀገሪቱ በቂ ምርት ባለመኖሩ፥ ያ ኩሩና ጨዋ ሕዝብ በየዓመቱ የፈረንጅ ተመጽዋች ሁኗል። በረኃብና በሽታ የሚያልቀው ጎልቂ መሳፍረት የለውም። በንጉሡ ዘመነ መንግሥት የተባይ ማጥፊያ መድኃቀኒት እየተረጨ ወባ ( ንዳድ) ከመላ ሀገሪቱ ቋፍቶ ነበር። በነመለስ አገዛዝ ግን ሀገሪቱነየተባይ መፈልፈያ ምንጭ ሁናለች። የወባ ማጥፊያ መድኃኒት ባለመረጨቱ በመላ ሀገሪቱ ሕዝቡ በወባ በሽታ እየረገፈ ነው። እንደዚሁም በዘመን አመጣሹ ኤድሰ በሽታ እየረገፈ ነው።

ጀግናው የኢትዮጵያ ጦር ኃይል ሆይ!

እስቲ ያለፈውን ታሪክ ላስታውስህ። በታህሣሥ 1953 ዓም የክብር ዘበኛ ሠራዊት በአመራር ጉድለት ሀገሪቱ ወደኋላ በመቅረቷና የዲሞክራሲ ሥርዓት ባለመኖሩና የተቀናቃኝ ፓርቲ ባለመቋቋሙ፥ ከዚህም የተነሳ ፍፁም የአፄዓዊ ፈላጭ ቆራጭ አምባ ገነንነት በመስፈኑ፥ የሀገራቸውና የሕዝባቸው ወደ ጥፋት ጎዳና መሄድ አሳስቧቸው፥መፈንቅለ መንግሥት ሞከሩ። እንዲሁም በ1957 ዓም ከጦር ሠራዊት 4፥ ከክብር ዘበኛ 2፥ ከባህር ኃይል 2፥ ከፖሊስ ሠራዊት 2፥ የተውጣጡ ሀገር ወዳድ 11 መኮንኖች ( እኔም ያለሁበት) ሀገሪቱን ከሚጠብቃት አደጋ ለመከላከልና የተሻለ መንግሥት ለማቀቋቋም የሚቻልበትን ሁኔታዎች በማጥናት ላይ እንዳሉ መንግሥት ልትገለብጡ አሲራችኋል ተብሎ በሞት በሚያስቀጣ ወንጀለኛ መቅጫ ደንብ አንቀጽ 248 ተጠቅሶ ተከስሰው ወኅኒ ቤት በመታሰራቸውም አልተፀፀቱበትም። መጀመሪያውኑም በውይይታቸው ፈላጭ ቆራጭ ንጉሡን በአንደኛው ሚዛን በማስቀመጥ ሀገሪቱንና ሕዝቡን በሁለተኛው ሚዛን ላይ

አስቀምጠው፥ሲለኩት ሚዛኑ ወደ ሕዝብ ስለአጋደለ ዓዔአዊው መንግሥት መወገድ ይገባዋል ከሚል ግምጋሜ ላይ ደርሰው ነበር። ምንም እንኳን ወታደር ከፖሊቲካ ውስጥ አይገባም የሚለውን የገዥዎችን መመሪያ ለመጣስ መኮንኖቹ የተገደዱት በሀገሪቱ ላይ አደጋ ሲያነብዣብብ በማያታቸው አደጋውን ቀድሞ ለመከላከል ነበር።

በየካቲት 1966 ዓም የጦር ኃይሎች በሙሉ የተሳተፉበት ተቃውሞን ያነሳሳውም የሀገሪቱ ወደ ኋላ መቅረት ነበር። ምንም እንኳን ንጉሡ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ቢሆኑም ሠራዊቱ መሪያችንን አንቃወምም አላለም።ከንጉሡ ይልቅ የሀገሪቱን ጥቅም ማስቀደም አለብን ብሎ ሁሉም ተስማምቶ በመንቀሳቀስ ንጉሡን ያለምንም ችግር ከሥልጣን አወረዷቸው። ሰላማዊ ለውጥ ተደርጎ ነበር።

አሁንም የሀገሪቱን ዳር ድንበር በመጠበቅ ላይ ያላችሁ የጦር ኃሎችሀገራችሁ በተለያዩ ችግሮች የተወጠረችው ልምድና ችሎታ በሌላቸው በነመለስ ዜናዊ ቡድን በመመራቷ በመሆኑ ችግሩ ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ ነው። የነመመለስ ዜናዊ/ ቡድን በጎሳ ትምክህተኝነት ሌሎቹን በጥላቻና በንቀት የሚዩ በከፋ ጭቆናና ብዝበዛ ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ታውቀዋለህ።

ቡድኑ የፖለቲካ ብስለት ስለሌለው ፖለቲካን ከኢኮኖሚው ከሰይንሳዊነት አውጥቶ በክልል ሰንሰለት ቀይዶታል። የማደግና የመስፋፋት ዕድል የለውም። በአንድ መልከአ-ምድር የሚኖርን ሕዝብ በጋራ የታሪክ ሂደትና ሥነልቦናዊ አንድነት የተዋቀረን ሕዝብ ያለ ፈቃዱ የጎጥ መንግሥት በማቋቋም ያወጣው መመሪያ ኅብረተሰቡን ወደ ኋላ ጎትቶታል። የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ከ1966 ዓም በፊት ከነበረበት ደረጃ ወርዷል። የሕብረተሰብም ይሁን ብሔራዊ ድጋፍ የሌለው፥ የሕዝብ ድጋፍ የተነፈገው፥ብቻውን ከላይ የተንከረፈፈ በመሆኑና በክፋት ሁለንተናዊ ባሕርዩ እያደረገ፥ እኛን አልመረጣችሁም እያለ በሕዝቡ የበቀል ርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛልና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ገፍትረህ ጣለው። ሕዝቡንም ከዘረኛ ሥርዓት ነፃ አውጣው። ሀገሪቱንም ከአንዣበባት አደጋ አድናት። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ሀገሩን ከውጭ ጠላት መከለሰከል ብቻ ሳይሆን፥ በሀገር ውስጥ ያለውን ጭቆና፥ ንቅዘትንና ሙስናን በማስወገድ በሚደረገው የዴሞክራሲ ትግል ሕዝቡን ነፃ የማውጣት ትግል የዜግነት ግዴታና ኃላፊነት አለብህ።

ጦሩ ተሰብስቦ ( ለመለስ ዜናዊ) ቢደረድ መላ፥
እምቢያለ ሚዛኑ ወደ ሕዝብ አደላ።
ጥንትም አንተ ነበርህ ዛሬም የለ ሌላ፥
ተነሳ ሠራዊት እርስ በርስ ሳይብላላ።
መድኃኒት ፍለጋ ዓለምን ሲዞሩ፥
ከጦር ኃይል ተገኘ የመዳኀኒት ስሩ፥
ነቃቅሎ የሚያጠፋ ከነ ዘር ማንዘሩ።

<u>ሀገርንና መሪዎችን ለያይቶ ስለ መፈረጅ</u>

1. የሀገር መሪዎችና ከበርቴዎች ታይተው ይጠፋሉ።

2. ሀገርና ሕዝብ ታሪክና ባኅል ግን ለዘለዓለም ይኖራሉ።

3. አምባገነናዊ የብዝበዛና ጭቆና ሥርዓት ይሻራል።

4. ዘረኝነትና ጎሰኝነት ድንቁርናና ኋላ ቀርነት ይጠፋሉ።

5. ዕውነትና ፍትኅ ለዘለዓለም ፀንተው ይኖራሉ።

6. ውሸትና ጎጠኝነት ፈጽሞ ይደመሰሳሉ።

ስለዚህም ከመቅጽበት ታይቶ ከሚጠፋ፥ ከሚሞትና ከሚረሳ ጋር ሳይወግኑ፥ ለዘለዓለም ጸንቶ ከሚኖር ከማይሞትና ከማይረሳ ሕይወት ካለው ከዕውነትና ከፍትኅ ጋር መቆም ይገባል። 15 የሚሆኑ የወያኔ ያመራር ቡድን በመለስ ዜናዊ ጠቅላይ ሚኒስትርነት በነጋ ወልደ ሥላሴ አማካሪነት በሕገ ወጥ መንገድ ሥልጣን ከያዙበት ግዚያት አንስቶ ሁለጊዜም የሚያስቀድሙት የራሳቸውን ግላዊ ጥቅም ብቻ ነው። ሀገሪቱን እየዘረፉና እየመዘበሩ በሥልጣን ለመቆየት እንጂ በየቦታው ለአሰማሩት ሠራዊት ፈጽሞ አያስቡለትም። ይህ ፈጽሞ ኃላፊነት የማይሰማው የጥፋት መልዕክተኛ ቡድን፥ የስለላ መረብ ዘርግቶ በውኃ ቀጠነ፥ሰላማዊ ንፁኃን ዜጎችን እያሰረ ማሰቃየትና መግደልን እንደ ልማት ቆጥሮ ይመፃደቅበታል።

ቡድኑ፥ ኢትዮጵያን ለራሱ መጠቀሚያ ካልሆነ በስተቀር ለእርሷ ክብርና ሉዓላዊነት፥ ለዕድገቷና ለብልፅግናዋ ደንታ የለለው መሆኑን በሽፍትነት ሳለ ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል በጽሁፍ የገለጸውን በተግባር ላይ አውሎታል።

ለሀገራችሁ ሉዓላዊነትና ለወገናችሁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብርና ነፃነት ሕይወታችሁን ሰጥታችሁ በየቦታው የምትዋደቁ የጦር ኃይሎች ሆይ!

የሚፈስሰው ደማችሁ፥ የሚንቆረቆረው ላባችሁና የሚከሰከሰው አፅማችሁ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያለመልም መስኖ መሆን ይገበዋል እንጅ ነገ ለማይኖርና ከድቶ ለሚጠፋ ለመለስ ዜናዊ ብላችሁ ገንዘብ መሰብሰቢያ መሳርያ አትሁኑ።

የጦር ኃይሉ በይሉኝታ ወይም በየዋኅነት በሥልጣን ላይ ያለው የመለስ ዜናዊ ቡድን ሲያጠፋ ዝም ብሎ ማየት ኃላፊነትን መዘንጋት ብቻ ሳይሆን የሞራል ውድቀትም ጭምር ነው።

<u>ጀግናው ሠራዊት ሆይ!</u>

መሣሪያ እያለህ፥ መምቻ፥ መግረፊያ ጡንቻ እያለህ፥ አዞሪ ማያ አንገት እያለህ እንዴት መተብ ማሰር አልቻልክም? ሀገር ጥሎ መኮብለል ለጦር ሰው ( ለወታደር) አያምርበትም የነ መለስ ዜናዊን የጭቆና አገዛዝ ተቃውሞ እየኮበለሉ የኢትዮጵያ ጠላት ወደ ሆነው ወደ ሻዕቢያ መሔድ በታሪክ የሚያስጠይቅ ብርቱ ወንጀል ነው። ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚያሴር ማን ሆኖ ነው ወደ ሻዕቢያ የሚኬደው? ይኸማ ከዕሾህ ወጥቶ ጋሬጣ አይሆንም?

ሲቪሉ የሚሰደደው ስለአልታጠቀና ስለአልተደራጀ ብሎም በወያኔ ነፍሰ-ገዳይ ቡድን በአጋዓዚ ስለሚጨፈጨፍ ነው። የጦር ኃይሉ ግን የተደራጀና የታጠቀ በመሆኑ፥ በኃይሉ መጠቀም ይገባዋል እንጅ፥ መኮብለል ወንጀል ነው። የመንግሥቱ ኃይለማራያምን ፈለግ ተከትሎ መኮብለል፥ በታሪክና በህግ እንዲሁም በሚመጣው ትውልድ ያስፈርጃል። አሳፋሪም ነው። የኢትዮጵያ ሀገራችሁ ጋራና ሸነብተረር፥ ጫካና ሸለቆ እያለላችሁ እስቲ ለሻቢያ እየሄዱ እጅ መስጠት ምን ይባላላ? ለሰሚውም ግራ ነው።የሠለጠነንና

የታጠቀ ሠራዊት ጥሎ ቢኮበልል፥ እነ መለስ ዜናዊን አይጎዳም። በኮበለለው ሠራዊት ምትክ አዲስ ይቀጥራሉ። የሚጎዳው ሀገርንና በችግር ላይ ያለውን ሕዝብ ብቻ ነው።

<u>የኢትዮጵያ ጦር ኃይል ሆይ!</u>

በሚደርስብህ በደልወድ ውጭ ሀገረ. መሰደዱን ትተህ፥ እርስ በእርስህ ተስማምተህና ተባብረህ እነ መለስ ዜናዊን ከሥልጣን አውርደህ ሀገርህን ከጥፋት አድን። ደመዎዝ ከሚከፍልህ ከሕዝብ ጋር ወግን።ለራስህም ይሁን ለቤተሰብህ ደስታ የምታገኘበት ነውና!

1ኛ. ሁሉንም ዜጎች እኩል የሚያስተናግድ መንግሥት ይመሥረት።

2ኛ. በሀገሪቱ ሕዝባዊና ፍትኃዊ የሆነ መንግሥት ይቋቋም።

3ኛ. በዱር በገደል ያለውና የከፋው ሁሉ ይሰብሰብ።

4)ኛ. በዓለም ዙሪያ የተሰደደው ሁሉ ወደ ሀገሩ  ወደ ኢትዮጵያ ።

በዓለም ሁሉ የተበተነው ስይንቲስቱ፥ መሐዲሱ፥ ኤኮኖሚስቱ፥ የሕግ ምሁሩ፥ የሕክምና ዶክተሩ፥ ሕዝብ የሚያደራጁ ምሁራን( Sociologists) እና ልዩ ልዩ የሙያ ትምህርት የተማሩ፥ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተቋቁሞ ነፃ ሁነው ያለ ምንም ተፅዕኖ ቢሠሩ ኢትዮጵያን ከመቅዕበት ገንብተውና አበልፅገው ተዓምራዊ ዕድገት ማሳየት ይችላሉ። ወደ ውጭ ሀገር የተሰደዱት ኢትዮጵያውያን ብዙ ዕውቀት የቀሰወሙ ስለሆነ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ ሀገሪቱን ካለችበት ውስብስብ ችግር አላቅቀው ከበለፀጉት ሀገሮች ቁጥር ውስጥ ሊያስገቧት ይችላሉና የጦር ኃይሉ በጉዳዩ አስቦበት፥ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም መጣር ይገባዋል።